በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትምህርት ሚኒስቴር

**FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**Ministry of Education**

| | |
|---|---|
| ***መመሪያ ቁጥር…………….*** | **Directive Number--------------** |
| <u>**የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የጥራት ኦዲት መመሪያ**</u> | <u>**Quality Audit Directive for Higher Education and Technical and Vocational Education and Training Institutions**</u> |
| የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ ሲቋቋም አንዱ የጥራት ማረጋገጫ ዘዴ የጥራት ኦዲት ሲሆን ኤጀንሲው በበርካታ ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት ሲያከናውን የቆየ ቢሆንም፤ አዋጁ ተቋማቱን ተጠያቂ የሚያደርግ የህግ ድንጋጌ ስለሌለው፣ አብዛኞቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በጥራት ኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡ ምክረ ሃሳቦች መሰረት የውስጥ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓታቸውን ያላሻሻሉ በመሆኑ፣ | Whereas, when the Higher Education Relevance and Quality Agency was established under the Higher Education Proclamation No. 351/2003, one of the quality assurance methods was quality audit, and the agency has been conducting quality audit at many institutions; however, since the proclamation does not contain any legal provisions holding institutions accountable, most higher education institutions have not improved their internal quality assurance systems in accordance with the recommendations made based on the findings of the quality audit; |
| የባለስልጣኑን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፳ሺ፲፬ የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት እንደሚያከናውን የተደነገገ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፳ሺ፲፩ አንቀጽ ፳፩ (፮) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በባለስልጣኑ የሚሰጡ ምክረ ሀሳቦችን የመተግበር ግዴታ እንዳለባቸው የሕግ አግባብ የተቀመጠ በመሆኑ፣ | Whereas, the Council of Ministers Regulation No. 515/2022, which was issued to determine the powers and functions of the Authority, stipulates that quality audits shall be conducted on Higher Education and Technical Vocational Education and Training Institutions, and Article 21 (6) of the Higher Education Proclamation No. 1152/2019 stipulates that Higher Education Institutions are legally obliged to implement the recommendations made by the Authority; |

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ እና በደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬ በበቂ ሁኔታ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በመኖራቸው፣

Whereas, there are issues not adequately covered by Proclamation No. 1152/2019 and regulation no 515/2022;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፲፱ (፬) መሰረት ይህ መመሪያ ተደንግጓል::

Now, this directive is issued in accordance with Article 19 (4) of Proclamation No. 1263/2021 which was issued to provide for the definition of the powers and duties of the executive organs of the federal democratic republic of Ethiopia.

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የጥራት ኦዲት መመሪያ ቁጥር -------/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 1. Short Title

This directive may be cited as “Higher Education and Technical and Vocational Education and Training institutions Quality Audit Directive No.------/2025”.

### ፪. ትርጓሜ

በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩፣ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬ እና የቴክኒክና ሙያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፶፬/፪ሺ፰ ላይ የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም

### 2. Definitions

Notwithstanding provisions of Higher Education Proclamation Number 1152/2019, the Council of Ministers Regulation No. 515/2022 and Technical and Vocational Education and Training Proclamation No. 954/2016, unless the context otherwise

| | |
|---|---|
| የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡- | requires: |
| ፩) **“ደንብ”** ማለት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬ ነው፤ | 1) “**Regulation**” means the regulation enacted by Council of Ministers to designate the organization, power and responsibility of FDRE Education and Training Authority, Regulation No 515/2022; |
| ፪) **“ተቋም”** ማለት የመንግስት ወይም የግል የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጥ ተቋም ነው፤ | 2) "institution" means a public or private higher education or technical and vocational institution that provides education and training; |
| ፫) **“የከፍተኛ ትምህርት”** ማለት በቅድመ እና ድህረ ምረቃ ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት ነው፤ | 3) “**Higher Education”** means education provided at undergraduate and post graduate level; |
| ፬) **“የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና”** ማለት በሀገሪቱ ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ደረጃቸው ከከፍተኛ ትምህርት በታች በሆኑ መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና እንዲሁም የሙያ ብቃት ምዘና ስርአት ሲሆን መደበኛ ባለሆነ መልኩ የተገኘን የሙያ ብቃት የማረጋገጥ ስርአትን ይጨምራል፤ | 4) **“Technical and Vocational Education and Training"** means a provision of technical and vocational education and training in any occupation, based on the country’s education and training policy, which is below higher education level through formal or non-formal means of training and education as well as process of assessing occupational competence and includes assessment of occupational competence that has been acquired through non-formal means; |
| ፭) **“ጥራት ኦዲት”** ማለት የትምህርትና ስልጠና ተቋም ወይም ፕሮግራም ውጤታማ የጥራት | 5) "**Quality Audit**” means an evaluation carried out at the institutional or program |

ማረጋገጫ ስርዓት ዘርግቶ እየተገበረ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

**፮)** “የውስጥ ጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት” ማለት ተቋማት  የትምህርት እና ስልጠና ጥራት ለማስጠበቅ የሚዘረጉት እና በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ  የውስጥ ጥራት ማስጠበቅ ስርዓት ነው፤

፯) **“ግለ-ግምገማ”** ማለት ተቋማት በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች መሠረት ራሳቸውን በመገምገም ጥንካሬና ክፍተቶቻቸውን የሚለዩበት ግምገማ ነው፤

**፰)** **“የግለ-ግምገማ ሪፖርት”** ማለት የተቋማትን አጠቃላይ የግለ ግምገማ ሂደት፣ ውጤትና በግለ ግምገማው የተገኙትን ክፍተቶች የሚያስተካክሉበት ቀጣይ እቅድ የያዘ ሪፖርት ነው፤

**፱)** **“የጥራት ኦዲት** ገለፃ” ማለት የጥራት ኦዲት ከመከናወኑ በፊት ለተቋሙ ስለ ጥራት ኦዲቱ ዓላማ፣ ሂደት እና ውጤት እንዲሁም ለጥራት ኦዲት ስለሚደረግ አጠቃላይ ዝግጅት የሚደረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ነው፤

level to make sure whether institutions have established and are implementing an effective internal quality assurance system;

6) "Internal quality assurance system" means a system established by institutions that should be continuously improved to ensure the quality of education and training;

7) "**Self-evaluation**" means an evaluation conducted by institutions themselves, based on Higher Education and Technical and Vocational Education and Training Quality Audit standards, to identify their strengths and weaknesses;

8) **“Self-Evaluation Report**” means a comprehensive report that details the self-evaluation process, findings and an improvement plan to address the identified gaps;

9) “**Quality Audit Briefing**” means a briefing provided to the institution before the quality audit is conducted, covering the audit procedure, objectives, expected outcomes, and preparations needed for the actual audit;

| | |
|---|---|
| ፲) **“የጥራት ማጎልበቻ እቅድ”** ማለት ተቋማት በግለ ግምገማ ሂደት የለዩዋቸውን ክፍተቶች እና በጥራት ኦዲት ግኝቶች መሰረት የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን ለማሻሻል የሚያዘጋጁት እቅድ ነው፤ | 10) "**Quality enhancement Plan**" means a plan developed by institutions to address the gaps identified through the self-evaluation process as well as recommendations made based on the findings of the quality audit; |
| ፲፩) **“ክትትል ግምገማ”** ማለት ተቋማት የጥራት ኦዲት ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን በሚጠበቀው ደረጃ መተግበራቸውን ለማረጋገጥ በባለስልጣኑ የሚደረግ ግምገማ ነው፤ | 11) "**Follow-up Evaluation**" means an evaluation conducted by the Authority to ensure that institutions implement the recommendations made based on the findings of quality audits to the expected level; |
| ፲፪) **“የጥራት ኦዲተሮች”** ማለት የባለስልጣኑ የጥራት ኦዲት ባሙያዎች እና በጥራት ኦዲተርነት ስልጠና የተሰጣቸው የውጭ የጥራት ኦዲት ባለሙያዎች ናቸው፤ | 12) “**Quality auditors**” means the Authority’s quality audit experts and external quality audit professionals who are trained to be quality auditors; |
| ፲፫) **“የኦዲተሮች ፓነል”** ማለት የጥራት ኦዲት እንዲያከናውን የተዋቀረ የኦዲተሮች ቡድን ነው፤ | 13) **“Auditors Panel"** means a team of auditors constituted to conduct a quality audit; |
| ፲፬) **“የጥቅም ግጭት”** ማለት በጥራት ኦዲት የግምገማ ሂደቱ ወይም ውጤቱ ላይ አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተፅኖ ሊፈጥር የሚችል በተቋማት እና በጥራት ኦዲተሮች መካከል የተፈጠረ ግንኙነት ነው፤ | 14) **“Conflict of Interest**” means a relationship between institutions and quality auditors that could potentially influence the quality audit process or outcome, either negatively or positively; |
| ፲፭) **“ምክረ ሀሳብ”** ማለት በጥራት ኦዲት ግኝቱ መሠረት ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዩች ላይ በባለስልጣኑ የሚሰጡ የማስተካከያ | 15) **“Recommendations”** means directions given by the Authority on areas that need improvement, based on the findings of the quality audit; |

ሀሳቦች ማለት ነው፤

፲፮) **"ዳግም ክትትል"** ማለት ውስን የጥራት አጠባበቅ ስርዓት ደረጃ ላይ በሚገኙ ተቋማት ላይ የሚደርግ የክትትል ግምገማ ነው፤

፲፯) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

**፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ፡-

፩/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም የመንግስት እና የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋምና ፕሮግራም፣

፪/ በፌደራል ደረጃ ለተቋቋመ እና ከውጭ ሀገር ለሚመጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣

ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ዋና ድንጋጌዎች</u>

**፬. <u>የተቋማት የውስጥ ጥራት ማጎልበቻ ስርዓት</u>**

፩/ ማንኛውም ተቋም በየጊዜው የሚሻሻል የውስጥ ጥራት ማጐልበቻ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፤

16) "**Re-Follow up"** means a follow-up evaluation conducted on institutions with "Minimally Functional" internal quality assurance systems;

17) Any expression in masculine shall include feminine expression as well.

**3. <u>Scope of Application</u>**

This directive applies to :

1/ Any public or private higher education institutions and program operating in Ethiopia;

2/ Foreign Technical and vocational education and training institutions functioning in Ethiopia, and those established at the federal level.

## <u>PART TWO</u>

## <u>Main Provisions</u>

**4. <u>Institutions' Inernal Quality Assurance System</u>**

1/ Any institution shall have an internal quality assurance system that is continuously improved;

፪/ ማንኛውም ተቋም በባለስልጣኑ የተለዩ ጠንካራ ጎኖችን የመጠበቅ ወይም የማሻሻል እና የተሰጡ ምክረ ሀሳቦችን መተግበር ይኖርበታል፡፡

2/ Any institution shall maintain or enhance the strengths identified by the Authority and act on the recommendations provided.

## ፭. የጥራት ኦዲት ጥያቄ ስለማቅረብ

የተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም ጥራት ኦዲት፡-

፩/ በባለስልጣኑ አነሳሽነት ወይም

፪/ በተቋማት ጥያቄ መሠረት

የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 5. Initiation of Quality Audit Request

Institutional or program quality audit shall be initiated either:

1/ By the Authority's initiative, or

2/ Upon the request of the institutions.

## ፮. የጥራት ኦዲት ጥያቄ ቅድመ ሁኔታዎች

የጥራት ኦዲት ጥያቄ በተቋም ወይም በፕሮግራም ደረጃ የሚያቀርብ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም በተቋም ደረጃ የሚያቀርብ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም፡-

፩/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፫ (፩) እና (፪) ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ አግባብነት ባለው አካል ትምህርት ወይም ስልጠና ለመስጠት የተቋቋመ ወይም ፈቃድ ያለው፤

፪/ ቢያንስ አንድ ዙር ተማሪዎችን ያስመረቀ፤

## 6. Pre-Conditions for Quality Audit Request

An institution of higher education requesting a quality audit at either the institutional or program level, or a Technical and Vocational Education and Training Institution requesting a quality audit at the institutional level:

1/ Shall be established or licensed by concerned body to provide education or training as indicated under Article 3(1) and (2) of this directive;

2/ Shall have at least one cohort of graduates.

## ፯. የጥራት ኦዲት መገምገሚያ ስታንዳርድ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊም ሆነ የፕሮግም እንዲሁም የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተቋማዊ የጥራት ኦዲት ግምገማ ባለስልጣኑ በሚያወጣው እና ቦርዱ በሚያፀድቀው ስታንዳርድና ውጤት አመላካቾች መሰረት ይከናወናል፡፡

## 7. Quality Audit Evaluation Standard

Institutional or program-based quality audits of Higher Education Institutions, as well as Technical and Vocational Education and Training Institutions shall be conducted based on standards and indicators issued by the Authority and approved by the board.

## ፰. ስለ ውጭ ጥራት ኦዲተሮች ምልመላ እና መረጣ

፩/ የውጭ ኦዲተሮች የሚመለምሉት እና የሚመረጡት ባለስልጣኑ በሚያወጣው እና ቦርዱ በሚያጸድቀው የውጭ የጥራት ኦዲተሮች የመመልመያ እና መረጣ ማንዋል መሠረት ይሆናል፤

፪/ የጥራት ኦዲት ግምገማ ላይ የሚሳተፉ የውጭ ኦዲተሮች የኦዲተርነት ስልጠና የወሰዱ ብቻ መሆን አለባቸው፤

፫/ የውጭ ኦዲተሩ ለኦዲተርነት ሲመለመል ኦዲት ከሚደረገው ተቋም ጋር የጥቅም ግጭት የሌለው መሆኑን ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 8. Selection and Recruitment of External Quality Auditors

1/ External auditors shall be recruited and selected in accordance with the External Quality Auditors' Recruiting and Selection Manual issued by the Authority and approved by the Board;

2/ Only trained auditors shall participate in the quality audit evaluation as external auditors;

3/ When the external auditor is recruited to be an auditor, he shall inform the Authority that he has no conflict of interest with the institution to be audited.

## ፱. ግለ ግምገማ

ተቋማት ግለ ግምገማ የሚያደርጉት ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው የግለ ግምገማ ማኑዋል መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡

## 9. Self-evaluation

Institutions shall conduct self-evaluation in accordance with the manual developed by the Authority.

## ፲. <u>ስለ ጥራት አጠባበቅ ስልጠና</u>

ተቋማት ስለ ትምህርትና ስልጠና ጥራት አጠባበቅ ስልጠና ከጠየቁ ባለስልጣኑ ስልጠናውን ይሰጣል፡፡

## ፲፩. <u>የጥራት ኦዲት ሪፖርት ህትመት</u>

፩/ የጥራት ኦዲት ሪፖርቱ ለባለድርሻ አካላት በባለስልጣኑ ተደራሽ እስኪደረግ ድረስ ሚስጥራዊነቱ ሊጠበቅ ይገባል፤

፪/ የፀደቀው የጥራት ኦዲት ሪፖርት ለባለድርሻ አካላት በባለስልጣኑ ተደራሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

## ፲፪. <u>ከአቻ ተቋማት ጋር በትብብር ስለመስራት</u>

፩/ የባለስልጣኑ የጥራት ኦዲተሮች በቀጠናው ወይም በአህጉር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ባሉ አቻ የጥራት አረጋጋጭ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ከሀገር ውጭ ባሉ የትምህርትና ስልጠና ተቋማት ላይ የጥራት ኦዲት ለማከናወን የውጭ ኦዲተሮች ፓነል አካል ሆኖ ሊሰራ ይችላል፣

## 10. <u>Quality Assurance Training</u>

If institutions request training on education and training quality assurance, the Authority shall provide the training.

## 11. <u>Publication of Quality Audit Report</u>

1/ The quality audit report shall remain confidential until it is made accessible by the Authority to stakeholders;

2/ The Authority shall make the approved quality audit report accessible to stakeholders.

## 12. <u>Collaboration with peer institutions</u>

**1/** The Authority's quality auditors may work as part of a panel of external auditors to conduct quality audits of education and training institutions abroad, in collaboration with peer quality assurance bodies at the regional, continental or international level.

## ክፍል ሦስት

## የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች

### ፲፫. የጥራት ኦዲት ፓነል ስብጥር

፩/ ተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም የጥራት ኦዲት ፓነል በባለስልጣኑ የጥራት ኦዲተር የሚመራ ሆኖ የውጭ የጥራት ኦዲተሮችን የሚያካትት ይሆናል፤

፪/ የጥራት ኦዲቱ የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይ የሚከናወን ከሆነ የሚሳተፉት የውጪ ጥራት ኦዲተሮች ኦዲት የሚደረገው የትምህርት መስክ ባለሙያዎች ብቻ ይሆናሉ፤

፫/ የጥራት ኦዲት ቡድን አባላት ተግባርና ሃላፊነት ባለስልጣኑ በሚያወጣውና ቦርዱ በሚያጸድቀው የውጭ የጥራት ኦዲተሮች መረጣና ምልመላ ማንዋል መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

### ፲፬. ግለ ግምገማ

፩/ በባለስልጣኑ የጥራት ኦዲት ስታንዳርድ መሰረት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተቋም ወይም በፕሮግራም ደረጃ እንዲሁም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በተቋም ደረጃ በየጊዜው ግለ-ግምገማ ማካሄድ ያለባቸው ሆኖ ለባለስልጣኑ የሚያቀርቡት ሪፖርት ለኦዲት

## PART THREE

## Procedural Provisions

### 13. Quality Audit Panel Composition

1/An institutional or program quality audit panel shall be led by the Authority's quality auditor and include external quality auditors;

2/ If the quality audit is conducted on a higher education program, the external quality auditors participating shall only be experts in the field of study being audited;

3/ The duties and responsibilities of quality audit panel members shall be determined in accordance with the selection and recruitment manual for external quality auditors issued by the authority and approved by the board.

### 14. Self-evaluation

1/ According to the Authority's quality audit standards, higher education institutions shall conduct periodic self-evaluation at the institutional or program level, as well as technical and vocational education and training institutions at the institutional level,

ማመልከቻ ባቀረቡበት ዓመት ያደረጉት ግለ ግምገማ መሆን ይኖርበታል፤

፪/ ተቋማዊም ሆነ የኘሮግራም የግለ ግምገማ ሪፖርት ሁሉንም ካምፓሶች ባካተተ መልኩ በተቋም ደረጃ መዘጋጀት ይኖርበታል፤

፫/ የግለ ግምገማ ሪፖርት በባለስልጣኑ እና በውጭ ኦዲተሮች ሚስጥራዊነቱ የተጠቀበ መሆን ይኖርበታል፤

፬/ ተቋሙ ያቀረበው የግለ ግምገማ ሪፖርት ማስተካከያ የሚያስፈልገው ከሆነ ባለስልጣኑ በሚያወጣው የጥራት ኦዲት ፕሮሲጀር ማንዋል መሰረት በሚሰጠው የጊዜ ገደብ አስተካክሎ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ በተሠጠው የጊዜ ገደብ አስተካክሎ ካላቀረበ የኦዲት ጥያቄውን  በራሱ ፈቃድ እንዳቋረጠ ይቆጠራል፡፡

## ፲፭. <u>የጥራት ኦዲት ገለፃ</u>

በማንኛውም ተቋም የጥራት ኦዲት ጉብኝት ከመከናወኑ  በፊት ስለ ጥራት ኦዲቱ ገለፃ ይደረግላቸዋል፡፡

and the report they submit to the Authority shall be the self-evaluation report they conducted in the year in which they submitted their application for audit;

2/ Both institutional and program-level self-evaluation reports shall include all campuses and be prepared at the institutional level;

3/ The Authority and external auditors shall maintain the confidentiality of the self-evaluation report;

4/ If the institution's submitted self-evaluation report requires amendments; the institution shall make the necessary adjustments and resubmit it within the timeframe specified in the Quality Audit Procedure Manual developed by the Authority. Failure to resubmit within the given timeframe will be considered a withdrawn request at the institution's discretion.

## 15. <u>Quality Audit Briefing</u>

Before conducting a quality audit visit in any institution, briefing on the quality audit shall be provided.

**፲፮. <u>የጥራት ኦዲት ማከናወን</u>**

፩/ ተቋማዊም ሆነ የፕሮግራም የጥራት ኦዲት በተቋም ደረጃ የሚደረግ ሆኖ ተቋሙ ከአንድ በላይ ካምፓሶች የሚኖሩት ከሆነ ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው የጥራት ኦዲት ፕሮሲጀር ማንዋል መሠረት የተመረጡ ካምፓሶች ላይ ኦዲት ይከናወናል፤

፪/ እንደ አስፈላጊነቱ ባለስልጣኑ ከጥራት ማስጠበቂያ የትኩረት መስኮች ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት ላይ ብቻ መሰረት በማድረግ የጥራት ኦዲት ሊያከናውን ይችላል፤

፫/ የጥራት ኦዲት ፓነሉ በተቋሙ የቀረበውን የግለ ግምገማ ሪፖርት ትክክለኛነት ሰነዶችንና መረጃዎችን በመመርመር፤ ከተቋሙ ማህበረሰብ ጋር በመወያየት እና በአካል ምልከታ በማድረግ መረጃ መሰብሰብና ማጠናቀር ይኖርበታል፤

፬/ ተቋሙ በጥራት ኦዲት ፓነሉ የሚጠየቁ መረጃና ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፣

**፲፯. <u>የጥራት ኦዲት ሳይክል(ዑደት)</u>**

የጥራት ኦዲት የተደረገ ተቋም በየአምስት አመቱ በድጋሚ መደረግ ይኖርበታል፡፡

16. **<u>Conducting Quality Audit</u>**

1/ Institutional and program quality audits are conducted at the institution level, and if the institution has more than one campus, audits shall be conducted on selected campuses in accordance with the quality audit procedure manual prepared by the Authority;

2/ The Authority shall conduct quality audits, as deemed appropriate, focusing on one or more areas of the standard;

3/ The quality audit panel shall validate the information in the self-evaluation report by reviewing documents, engaging in discussions with the institution's community, conducting on-site observations, and collecting and analyzing relevant data;

4/ The institution shall provide the information and evidence requested by the quality audit panel.

**17. <u>Quality Audit Cycle</u>**

An institution that has undergone a quality audit shall be re-audited every five years.

| | |
|---|---|
| **፲፰. <u>የጥራት ኦዲት ሪፖርት ዝግጅት</u>** | **18. <u>Quality Audit Report preparation</u>** |
| ፩/ እያንዳንዱ ስታንዳርድ ሪፖርት ሊጠናቀርበት ይገባል፤ | 1/ For each standard report shall be compiled; |
| ፪/ ተቋሙ ከተቀመጠው ስታንዳርድ በላይ አፈፃፀም ያሳየ ከሆነ እንደ መልካም ተሞክሮ ይወሰዳል:: | 2/ If the institution performs above the established standards, it shall be considered as commendation; |
| ፫/ ተቋሙ ከተቀመጠው ስታንዳርድ በታች አፈፃፀም ያሳየ ከሆነ የማሻሻያ ምክረ ሀሳብ ሊሰጥበት ይገባል፤ | 3/ If the institution has performed below the established standard, a recommendation for improvement shall be made; |
| ፬/ ሪፖርቱ በባለስልጣኑ የጥራት ኦዲት ፕሮሲጀር ማንዋል መሰረት ብቻ ይዘጋጃል፤ | 4/ The report shall be prepared solely in accordance with the Authority's Quality Audit Procedure Manual; |
| ፭/ ረቂቅ ሪፖርቱ ተቋሙ ግብረ መልስ እንዲሰጥበት መላክ ይኖርበታል፤ | 5/ The draft report shall be sent to the institution for feedback; |
| ፮/ ተቋሙ የተላከለት ረቂቅ ሪፖርት ላይ ግብረ መልስ ባለስልጣኑ በሚወጣው የኦዲት ፕሮሲጀር ማንዋል ላይ በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ ሪፖርቱን ሙሉ ለሙሉ እንደተቀበለው ይቆጠራል፡፡ | 6/ If the institution fails to provide feedback on the draft report within the time frame outlined in the audit procedure manual issued by the authority, the report shall be deemed accepted by the institution. |
| **፲፱. <u>ስለ ጥራት ኦዲት ክትትል ግምገማ</u>** | **19. <u>Quality Audit Follow-up Evaluation</u>** |
| ፩/ የጥራት ኦዲት ረቂቅ ሪፖርቱ ለተቋሙ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀ የጥራት ማጎልበቻ እቅድ በኦዲት ፕሮሲጀር ማንዋል ላይ በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይኖርበታል፤ | 1/ Once the draft quality audit report is officially communicated to the institution, the institution shall submit a quality enhancement plan, prepared at the institutional level, to the Authority within the timeframe specified in the Quality Audit Procedure Manual; |

፪/ የጥራት ኦዲት ፕሮሲጀር ማንዋል ላይ በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የጥራት ኦዲት የተከናወነባቸው ተቋማት ላይ የክትትል ግምገማ ይደረጋል፤

፫/ ተቋሙ ከአንድ በላይ ካምፓሶች የሚኖሩት ከሆነ በተመረጡ ካምፓሶች የክትትል ግምገማ የሚደረግ ሆኖ ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ፕሮሲጀር ማንዋል መሰረት ካምፓሶች ይመረጣሉ፡፡

**፳. <u>የጥራት ኦዲት አፈፃፀም ደረጃዎች እና</u>**

ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ውጤታማነት መሠረት ሙሉ ለሙሉ የሚሠራ፣ የተሟላ  እና  ውስን የውሰጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ያላቸው በመባል በሦስት የውስጥ ጥራት አጠባበቅ የውጤታማነት ደረጃዎች የሚመደቡ ሲሆን ውጤቱ በሚሰጠው የምስክር ወረቀት የሚገለፅ ይሆናል፡-

፩/ በእያንዳንዱ የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የጥራት ኦዲት ጋይድላየኖች ሙሉ ለሙሉ ተሟልተው ሲገኙ እና ጥቂት ጋይድላየኖች ብቻ በከፊል የተሟሉ ሲሆን የጥራት ኦዲት ለተከናወነበት የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋም የሚሰጠው የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ደረጃ  ሙሉ ለሙሉ የሚሠራ ይሆናል፤

**2/** A follow-up evaluation shall be conducted on institutions where a quality audit has been conducted, according to the time frame set out in the Quality Audit Procedure Manual;

3/ If the institution has more than one campus, quality audit follow up evaluation shall be conducted on campuses that are selected based on the quality audit procedure manual.

**20. <u>Quality Audit performance level</u>**

Based on the effectiveness of their internal quality assurance system, audited institutions are classified into three levels: “Fully Functional”, “Functional” and “Minimally Functional.” The results shall be communicated through certification:

1/ When most of the quality audit guidelines outlined under each quality audit standard are “Fully Compliant” and only a few guidelines are “Compliant”, the internal quality assurance system level of the higher education or technical and vocational training institution where the quality audit was conducted shall be “Fully Functional.”

፪/ በእያንዳንዱ የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የጥራት ኦዲት ጋይድላየኖች ተሟልተው ሲገኙ እና ጥቂት የጥራት ኦዲት ጋይድላየኖች ብቻ ያልተሟሉ ሲሆን የጥራት ኦዲት ለተከናወነበት የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የሚሰጠው የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ደረጃ የተሟላ ይሆናል፣

፫/ በእያንዳንዱ የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች ስር የሚገኙ አብዛኞቹ የጥራት ኦዲት ጋይድላየኖች ያልተሟሉ ሆነው ሲገኙ የጥራት ኦዲት ለተከናወነበት የከፍተኛ ትምህርት ወይም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም የሚሰጠው የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ደረጃ ውስን ይሆናል፣

፬/ ውስን የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ያላቸው ተቋማት አንድ ጊዜ የዳግም ክትትል ግምገማ ሊደረግላቸው የሚገባ ሆኖ በዳግም ክትትሉ የተሟላ የጥራት አጠባበቅ ደረጃ ላይ የማይደርሱ ከሆነ የኦዲት አፈፃፀም ውጤቱ ለፈቃድ እድሳት ውሳኔ ግብዓት የሚውል ይሆናል፡፡

2/ When most of the quality audit guidelines outlined under each quality audit standard are “Compliant” and only a few quality audit guidelines are “Non-compliant,” the level given to the internal quality assurance system of the higher education or technical and vocational training institution where the quality audit was conducted shall be considered as “Functional” internal quality assurance system;

3/ When the majority of the quality audit guidelines outlined in each quality audit standard are “Non-compliant” the level given to the internal quality assurance system of the higher education or technical and vocational training institution where the quality audit was conducted shall be considered as “Minimally Functional”;

4/ Institutions with “Minimally Functional” internal quality assurance systems shall undergo a one-time re-follow up evaluation. If they do not achieve the level of “Functional” internal quality assurance during the re-follow up, the results will be used as input for license renewal decision.

፭/ የጥራት ኦዲት አፈፃፀም ደረጃ የምስክር ወረቀት በሦስት ቀለማት የሚገለፅ ሆኖ ሙሉ ለሙሉ ለሚሠራ የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ያለው ተቋም በአረንጓዴ፣ የተሟላ የጥራት አጠባበቅ ስርዓት ያለው ተቋም በቢጫ እና ውስን የውስጥ ጥራት አጠባበቅ ስርዓት ያለው ተቋም በቀይ ቀለም የሚወከል ይሆናል፡ ፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፳፩. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት

በዚህ መመሪያ እና በከፍተኛ ትምህርት እና በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የጥራት ኦዲት ስታንዳርዶች መሰረት የጥራት ኦዲት ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው የትምህርትና ስልጠና ተቋም የኦዲት ሪፖርቱ ተደራሽ በሆነ በ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል ባለስልጣኑ በ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡

### ፳፪. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩/ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ እና በደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬ መሰረት የተከናወኑ የጥራት ኦዲት በዚህ መመሪያ መሰረት እንደተከናወኑ ተደርገው ይቆጠራሉ።

5/ The quality audit performance level certificate given to audited institutions shall be represented in three colors: green for institutions with a “Fully Functional” internal quality assurance system, yellow for those with “Functional “quality assurance system, and red for institutions with “Minimally Functional” internal quality assurance system.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 21. Grievance and Resolution Procedure

In accordance with this directive and the quality audit standards for higher education and technical and vocational training institutions, an education and training institution may submit an appeal regarding the quality audit decisions to the Authority within 30 days of the audit report being accessible. The Authority shall respond within 30 days.

### 22. Transitory Provisions

1/ Quality audits carried out in accordance with Proclamation No. 1152/2011 and Regulation No. 515/2014 shall be deemed to have been carried out in accordance with this directive.

| | |
|---|---|
| ፳፫. **<u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>**<br>ይህን መመሪያ ትምህርት ሚኒስቴር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡<br><br>፳፬. **<u>መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ</u>**<br>ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በትምህርት ሚኒስቴር ድረ ገፅ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ከሆነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡<br><br>**አዲስ አበባ 2017**<br><br>**ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)**<br><br>**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር** | 23. **<u>Amendment of the Directive</u>**<br>The Ministry of Education may amend this directive when it is necessary.<br><br>**24. <u>Effective date of the Directive</u>**<br>This guideline will come into effect from the date it is registered with the Ministry of Justice and made available to the public on the Ministry of Education's website.<br><br>**Addis Ababa 2025**<br><br>**Berhanu Nega (Professor)**<br><br>**Minster, Ministry of Education of the Federal Democratic Republic of Ethiopia** |